# ጥርሱን አግጦ ለወጣ የአምባገነኖች የምርጫ ለበጣ ምላሹ "እምቢ ለሙብቴ!!!" ብቻ ነው

ከግንቦት7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የተሰጠ መግለጫ

ግንቦት 17 2002 ዓ.ም

ውርደት ውርደት ውርደት፤ ማለቂያ የሌለው ውርደት:: የሃገር ውርደት፣የዜጎች ውርደት፣ የሃይማኖት፣ የሽምግልና እና የፍትህ ተቋማት ውርደት። የድህነት፣ የልመና የስደት ውርደት። የታሪክ፣ የባንዲራና የሃገር ውርደት:: የወያኔ አምባገነናዊ ዘረኛ አገዛዝ ስልጣን ከያዘበት እለት ጀምሮ ለሃገራችንና ለህዘቧ በገፍ ሲያመርትላቸው የኖረው ውርደትን ብቻ ነው:: በወያኔ ዘመን ያልተዋረደና ያልረከሰ የማንነታቸን መሰረት የነበረ እሴትና ተቋም አይገኝም። በመለስ ዜናዊ የሚመራው ዘረኛ አገዛዘ የቆመበት ጸረ ኢትዮጵያና ጸረ ኢትዮጵያውያንን አስተሳሰብ አገዛዙ በዜጎች ላይ ለሚያሳየው ንቀትና ጥላቻ ለሚፈጽማቸው የማዋረድ ድርጊቶች ዋናው ምክንያት ነው።

በምርጫ ስም ሰሞኑን ወያኔ የፈጸመው አስነዋሪ ድርጊት ባለፉት 19 ዓመታት ሲያሳየን የኖረው የንቀትና የውርደት ስልጠናው ከፍተኛው መገለጫ ነው:: የመለስ ዜናዊ ዘረኛ ቡድን በኢትዮጵያ ህዝብ የ1997 ምርጫ ታሪካዊ ክንዋኔ እንዲኮራ ሊያደርገው የሚያስቸል ምንም ዓይነት ህዝባዊና ሃገራዊ ትስስር የሌለው በመሆኑ በህዝብ ክንዋኔ መርካትን ሳይሆን መከፋትን እንዲመርጥ ሆኗል። ወያኔ ስልጣንን ከህዝብ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ውጭ ለአምስት ዓመታት በጉልበቱ ይዞ በ1997 ምርጫ በድምጹ የቀጣውን ህዝብ ለማዋረድ ያዘጋጀውን ታላቅ ድግስ እነሆ በሰሞኑ የ2002 የፌዝ ምርጫ ይዞ ብቅ አለ::

የግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የሰሞኑን የወያኔ የምርጫ ለበጣ ወያኔ ሃገሪቱንና ህዝቧን ለማዋረድ ያዘጋጀው ቋሚ መርሃ ግብር ቀጣይ ድርጊት ነው ብሎ ያምናል:: የአስመሳዩ ምርጫ ዓላማ ምን ታደርጉኛላችሁ በሚል እብሪት ተሞልቶ የኢትዮጵያ ህዝብ ለሰላሜና ለብልጽግናዬ፣ ለአንድነቴና ለነጻነቴ ዋስትና ይሆናል ብሎ ተሰፋውን በጣለበት የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ህልሙ ላይ በብልግና የተሞላ እጣቢ መድፋት ነው::

ወያኔ ህዝብንና እንፎካከርሃለን ያሉትን የፖለቲካ ፓርቲዎች አፍኖ፣ በመደለል በማስፍራራት በመደብደብ በመግደል ያከናወነው የምርጫ ተውኔት ዓላማው ህዝብን መበቀልና ማዋረድ ብቻ ነው። በ1997 ምርጫ ወያኔ አንድ ድምጽ ለማግኘት በተቸገረባቸው ከተምችና ገጠሮች ራሱን የመቶ በመቶ ድምጽ አሸናፊ እያደረገ፣ በዓለም ላይ በአምባገነን አገዛዞቸ ስር የተደርጉ የቅጥፈት ምርጫዎቸን ሬኮረዶቸን ሰበርኩ ሲለን እታመናለሁ ብሎ ሳይሆን "እሰቲ የምትሆኑትን አያለሁ" የሚል በእብሪት የተሞላ ንቀቱን ሲገልጽልን ነው።

ከ547 የምክር ቤት መቀመጫዎች መሃል ለተቃዋሚ አንድ መቀመጫ ሰጥቶ 546ቱን አሸነፌኩ ይህንን ውጤት በጸጋ ያልተቀበለ ልብሱ እየወለቀ ይገረፋል ሲለን ቅስማቸሁን ሰብሬ አዋርጄ እገዛችኋለሁ ምንም ልታደርጉ አትችሉም እያለን ነው:: እንዲህ እይነቱ አዋራጅ ድርጊት ወያኔ ሲፍጸምብን የመጀመሪያው ባይሆንም ያሁኑ ልዩነቱ የወያኔን አዋራጅ ድርጊት ወደን የገባንበት ለመሆኑ በድምጻችን ያረጋገጥበት ማስረጃ አለኝ ማለቱ ብቻ ነው:: የ2002 ምርጫ ወያኔ በደፋው የአምባገነንነት ዘውድ ላይ ተራራ የሚያከል የእብሪት ፈርጥ ከመጫን ሌላ ትርጉም የለውም::

የወያኔ የማጭበርበር ምርጫ ያስነሳው አቧራ ሲጠራ ኢትዮጵያውያን ከፊታችን ቆሞ ያገኘነው አንድ ጥያቄ ብቻ ነው። “እንደ ሃገር፣ እንደ ህዝብና እንደ ሰብአዊ ፍጥረት ይህንን አዋራጅ ስርዓት እስከ መቼ ተሸክመን መቀጠል እንችላለን?” የሚለው ነው። በእንዲህ አይነቱ ውርደት ውስጥ የሚኖሩ ዜጎች የሚኖሩባት ሃገር እውን ሃገር መባል ትችላለችን፤ ነዋሪዎቿስ ዜጎች ተብለው መጠራት ይቻላሉን? ለመሆኑ እስከመቼ ነው ይህንን አዋራጅ ስርዓት እንዲቀጥል የምንፈቅድለት?

ዛሬ በመለስ ዜናዊ አማካይነት በሁላችንም ላይ የተጫነው ውርደት በፖለቲካ አመለካከትና በምንከተለው የትግል ስልት ልዩነት ልናድበስብሰው ከማንችልበት ደረጃ በላይ ተሸጋግሯል። የቋንቋ፣ የባህልና የእምነት ልዩነቶቻችንን እንቅፋት ሳይሆኑብን በጋራ ልንመክተው የሚገባ የመንፈስ ቁስል ሆኗል። ወቅቱ እያንዳንዱ ዜጋ እራሱን የሚመረምርበት፣ “እንዴት ራሴን፣ ቤተሰቤን፣ ማህበረሰቤንና ሃገሬን ለእንዲህ ዓይነቱ ውርደት አበቃሁ?” ብሎ ራሱን የሚጠይቅበት ወቅት ነው።

ወቅቱ ስብራታችንን የምናሽበት፤ ለራሳችንም የምናዝንበት ሊሆን አይገባም። ቅጥረኞች ለሚያኪያሂዱት ቅስም ሰባሪ ፕሮፓጋንዳ ጆሮዋችንን የምንከፍትበት ጊዜ ሊሆን አይገባም። ይልቁንስ ወቅቱ በወያኔ ማንነትና ምንነት ላይ የጋራ ግንዛቤ ይዘን በጋራ ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ምስረታ የምንነሳበት ነው። ከማንኛውም ነገር በላይ በወያኔ የተገፈፈውን ሰብዓዊ ክብራችንን ለማስመለስ “ውርደት በቃን” የምንልበት ነው።

ወያኔ ሰሞኑን በምርጫ ስም የፈጸመው ነውር የግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የጀመረውን ትግል ፍትሃዊነትና የሚከተለው ሁለገብ የትግል ስልት ትክክለኛነትን አረጋግጧል። እምቢ ለዘረኛወና አምባገነኑ ወያኔ በሚል እልህ ከሁሉም ሃገራችን የዴሞክራሲ ሃይሎች ጋር ተባብረን ወያኔን ከማስውገድ ውጭ በሃገራችን ዴሞክራሲን ማስፈን እንደማንችል አመላክቶናል።

የወቅቱ የግንቦት 7 የትግል ጥሪ: “የጋራ ውርደት እንዲያከትም እብሪተኞችን በጋራ እምቢ እንበል፤ ዘረኛውና አዋራጁን የወያኔ ስርዓት ለማስወገድ በጋራ እንነሳ!!!:” የሚል ነው።

**የግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ**